# የኢትዮጵያና የግብፅ አዲሱ የመግባቢያ ምዕራፍ

**ልዑል ነጋሲ 07/03/14**

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ እና የግብፁ አዲሱ ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አል-ሲሲ ከመሰንበቻው በኢኳቶሪያል ጊኒ መዲና ማላቦ ውስጥ በተካሄደው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ ላይ ተገናኝተው በተለያዩ ጉዳዩች ዙሪያ መግባባት ላይ ደርሰዋል። ይህ ታላቅ ዜና ነው። ታላቅ የዲፕሎማሲ ድልም ጭምር ነው—የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነት ወደ አንድ ደረጃ ከፍ ሊያደርግ የሚችል። መሪዎቹ በተለይም በዓባይ ወንዝ አጠቃቃምና በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ በዝርዝር ነጥቦች ላይ መግባባታቸውን የመገናኛ ብዙሃን በዘገባዎቻቸው አመልክተዋል፡፡ በውይይታቸውም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በፀጥታና በአካባቢያዊ ግንኙነቶች ላይ በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን የሁለትዮሽ ኮሚሽን ለማቋቋም ስምምነት ላይ የደረሱ ሲሆን፤ 'የዓባይ ወንዝ ለግብፅ ህዝብ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል፣ ለኢትዮጵያውያንም ከረሃብና ከድህነት አረንቋ የመውጣትና ያለመውጣት የሞት ሽረት የልማት ትግል ጥያቄ ነው' በሚለው ሃሳብ ላይም ተግባብተዋል፡፡

ከተግባቡበት ነጥቦች ውስጥ በዓባይ ወንዝ ጉዳይ ላይ የመነጋገርና የመተባበር መርህን ማስፈን፣ ለክልላዊ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠት ፋይናንስ በቀላሉ እንዲገኝ ማድረግ፣ የአካባቢውን የውሃ ፍላጎት ሚሚላትና እጥረቱንም መቅረፍ እንዲሁም ዓለም አቀፍ የህግ መርሆችን መቀበልና ማክበር የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡ ታላቁን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብን አስመልክቶም፤ ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን ጀምረው ያቋረጡትን የሦስትዮሽ ውይይትን በፍጥነት በመጀመር የዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ምክረ ሐሳብን ተግባራዊ ማድረግ፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ምንም ዓይነት ጉዳት በግብፅ የውኃ አጠቃቀም እንዲያደርስ፣ የግብፅ መንግሥት በገንቢ ውይይት እንዲገዛና የኢትዮጵያንም የልማት ፍላጎት እንዲያከብር እንዲሁም በሦስትዮሽ የጋራ ማዕቀፍ ውስጥ በቅን ልቦና መተባበር በሚሉት ነጥቦች ላይም ከስምምነት ላይ መድረሳቸው ተነግሯል፡፡

እርግጥ እነዚህ የመግባቢያ ነጥቦች ለሁለቱም ሀገሮች እኩል ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው። እኔ እስከሚገባኝ ድረስም የመግባቢያ ነጥቦቹ ለሁለቱ አገሮች ግንኙነት አዲስ ምዕራፍ የከፈቱ

ናቸው ተብለው ሊገለፁ የሚችሉ ናቸው፡፡ ምንያቱም ነጥቦቹ ሀገራቱን 'ሁሉም አሸናፊዎች' (win-win) እንዲሆኑና በጋራ ጥቅም ላይ በተመሰረተ ሁለንተናዊ ግንኙነት እንዲመሩ የሚያስችሏቸው ስለሚሆኑ ነው። እናም ስምምነቶቹ 'እሰየው' የሚያሰኙ በመሆናቸው፣ እንዲህ ዓይነቱ በጋራ ጥቅም ላይ ተባብሮ የመስራት ዝንባሌ ሊጎለብትና ሊበረታታ ይገባዋል ባይ ነኝ።

የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝቦች በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ የሚታወቁት ለሰላምና ለሰላም ብቻ የቆሙ እንዲሁም ቀደም ባሉት ስርዓቶች አንገታቸውን አስደፍቶ ለተመፅዋችነት የዳረጋቸውን ድህነት ድል ለመንሳት በሚያደርጉት ፈጣንና ተከታታይ ልማታዊ ዕድገትን የማስመዝገብ ዘመቻ ላይ ያሉ መሆናቸው ነው። እርግጥ ሀገራችንን ጨምሮ በርካታ የተፋሰሱ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጠውን የኢንቴቤውን የስምምነት ማዕቀፍ ከመፈረም አልፈው፣ በየሀገሮቻቸው ፓርላማዎች ለማስፀደቅ በዝግጅት ላይ ባሉበት በአሁኑ ወቅት እንዲሁም እንደ ፕሬዚዳንት አል-ሲሲ ዓይነት የጋራ ተጠቃሚነትን የሚቀበሉ ግብፃዊያን ፖለቲከኞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መምጣታቸው የዓባይም ይሁን የታላቁ የህዳሴ ግድብ ጉዳይ ቅቡል መሆኑን የሚያመላክት ነው።

ይሁንና በእኔ እምነት አሁንም ቢሆን በግብፅ በኩል ለስምምነቱ ተፈፃሚነት ቁርጠኛ መሆንን የሚጠይቅ ይመስለኛል። ምክንያቱም በሰለጠነው የ21ኛው ክፍለ-ዘመን ውስጥ እየኖሩ፣ በ19ኛው ክፍለ-ዘመን ውስጥ የሚገኙ ይመስል አሮጌ የታሪክና የቅኝ ግዛት ቅሪት እሳቤዎችን የሚያቀነቅኑ ውህዳን የቀደምት የግብፅ ስርዓት አቀንቃኞች ሁኔታውን በበጎ ዓይን ሊመለከቱት ይችላሉ ተብሎ ስለማይታሰብ ነው። ይሁንና "ብዙሃን ይመውኡ" እንዲል ግዕዙ፣ የሰለጠነን አመለካከትና ተግባርን የሚከተሉ በርካታ ግለሰቦች ባሉበት ሀገር ውስጥ የውህዳን ያረጀ ያፈጀ እሳቤ ቦታ ሊኖረው አይችልም። ለምን ቢባል፣ የእነዚህ ወገኖች የትናንት የተሳሳተ እሳቤና ተግባር ምንም ጠብ የሚል ነገር የሚታወቅ ስለሆነ ነው።

እንደሚታወቀው ዓለም በግሎባላይዜሽን የትስስር ድር እንደ አንድ መንደር በምትታይበት በዘመነው 21ኛው ክፍለ ዘመን ችግሮችን ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ ተግባብቶ መፍታት አንዱ የስልጣኔ መገለጫ ነው። ማናቸውም አለመግባባቶች ባህሪያዊና በሰው ልጅ መስተጋብሮች ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ክስተቶች በመሆናቸው መፍትሔያቸው

ፀረ-ዴሞክራሲያዊ መሆን እንደሌለበትም ይታመናል። እናም በማናቸውም ቦታ የሚከሰቱ አለመግባባቶች ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አካላት መካከል የሚከሰት በመሆኑ የመፍትሔ አማራጮች ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ወገኖች አሸናፊ የሚሆኑበት መንገድ እንጂ፣ ባለፉት አሮጌ ዘመናት አሳፋሪ ማንነት እየቆዘሙና ያረጀና ያፈጀ አስተሳሰብን እያቀነቀኑ አንደኛው በሌላኛው ላይ ቀረርቶና ፉከራ በማሰማት የጦርነት ነጋሪት በመጎሰም አሊያም እኩይ ሴራዎችን በመጎንጎን ተፈፃሚ የሚሆን አይደለም።

ይህን መሰሉ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምልከታም የትኛውንም ወገን ቢሆን አሸናፊ የማያደርግና የማይጠቅም ከመሆኑም በላይ፣ በዘመናዊው ዓለም ውስጥ በአላዋቂ ተጓዥነት መገለልን በማስከተል የሚያስከፍለው ዋጋ ከፍተኛ መሆኑ አይቀሬ ነው። “በትናንት በሬ ያረሰ የለም” እንዲል የሀገራችን አርሶ አደር፣ የትናንቱ አሮጌ አስተሳሰብ እንዳለቀ ሸማ ወልቆ መጣል ያለበት ትናንት ነው—ዛሬ ላይ እንኳንስ ቦታ ሊኖረው ቀርቶ አዳማጭም የለውምና። በተለይም ለዘመናት የአፍሪካንና የልጆችዋን ማንነት ሲያዋርድ፣ ልጆችዋን በባርነት ሲሸጥና ሲለውጥ እንዲሁም አንጡራ ሃብቶቿን ሲቦጠቡጥና ለራሱ ጥቅም ሲል መርዛማ ውሎችን ሲከትብ የኖረው የቅኝ አገዛዝ ኢ-ሰብዓዊ አስተሳሰብ በፀያፍነቱ ሳቢያ ዛሬ ላይ ከታሪክነት በዘለለ ሰሚ ጆሮ የለውም።

ይህን ፀረ-ሰውዓዊ እሳቤን ከላያቸው ላይ አሽቀንጥረው ለመጣልም አፍሪካውያን በተናጠልም ይሁን በቅንጅት ታግለዋል፣ ህይወታቸውንም ቤዛ አድርገዋል፣ ታስረዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ ቤት ንብረታቸውንም አጥተዋል– “ሰውነታቸውን” ከሰው በታች አውርዶ በመፈጥፈጥ እንዳሻው ሲያደርጋቸው የነበረውን አስከፊ ተግባር ከነ ግሳንግስ አስተሳሰቦቹ ለማስወገድ። እናም ይህ ዘረኛ ተግባር ዛሬ በአፍሪካ ልሳነ-ምድር እንኳንስ አስተሳሰቡ ገቢራዊ ሊሆን ቀርቶ የሚታሰብ አይደለም። ምንያቱም አርጅቶ የተቀበረው የቅኝ አገዛዝ እሳቤ በያኔው የአህጉሪቱ ድርጅትም ይሁን በአሁኑ ህብረት ውስጥ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ነው።

ይሁንና በአፍሪካ ካርታ ውስጥ የሌሉ የሚመስሉት አንዳንድ የግብፅ ውህዳኖች ይህን ለመላው አፍሪካ የውርደት ካባን ያጎናፀፈን የቅኝ አገዛዝ አስተሳሰቦችንና ውሎችን እያጣቀሱ፣ ከ21ኛው ክፍለ ዘመን የኋሊት በመንደርደር አሮጌውን አሳፋሪ ካባ አንስተው ለመጠቀም በመሻት ላይ ይገኛሉ። ይህም ጉዳዩን በአግራሞት በሚመለከቱ ወገኖች ዘንድ “አዲሶቹ የግብፅ መሪዎች እየኖሩ ያሉት በየትኛው ክፍለ-ዘመን ነው?” የሚል ጥያቄን

እንዲያነሱ አድርጓቸዋል። ታዲያ እነዚህ አንዳንድ የግብፅ የቀድሞ ገዥ መደብ ቅሪቶች ይህን ማንንም የማይጠቅም አስተሳሰብ ከማቀንቀን ባለፈም፣ ሀገራችን ከድህነት አዙሪት ቀለበት ለመውጣት ወንዞቿን ፍትሐዊና የተፋሰሱን ሀገራት ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ በአባይ ወንዝ ላይ የጀመረችውን የታላቁን የህዳሴ ግድብ በመቃወም፣ "እ.ኤ.አ በ1929 እና በ1959 በቅኝ ግዛት ዘመን ውሎች የተሰጠን የውሃ መጠን አንድም ጠብታ መነካት የለበትም" በማለት የህዝባችንን ከድህነት የመውጣት ጥረት ከድፍረት በመቁጠር ለማጣጣል ሞክረዋል። "ግድቡ እንዲቆም ኢትዮጵያ የምትገነባበትን ቁሳቁስ የምታስገባው በጂቡቲ በኩል ስለሆነ ጂቡቲን መያዝ አለብን" የሚል አስገራሚ ዲስኩር ከማሰማት ባለፈም ጦርነትን ጨምሮ ማንኛውም አማራጭ ክፍት እንደሆነ በመጥቀስ እኩይ ሴራዎችን ሲደረድሩ ሰንብተዋል።

በአደባባይ በተነገረው ሴራቸው መሰረት ግድቡን ማስቆም ይችሉ ዘንድ፣ ሰላዮችን ያሰማራሉ፣ ሀገራችንን ለማዳከም ከአጎራባች ሀገሮች ጋር ያናቁራሉ፣ ተቃዋሚ ሃይሎችን ይደግፋሉ። ይህ ብቻ አይደለም–እነዚህ አማራጮች ካልተሳኩም በግድቡ ላይ ቀጥተኛ ጥቃት መሰንዘር ይገባል እስከሚል የጦርነት ሃሳብም መድረሳቸው አይዘነጋም። እርግጥ ሚዛናዊ አስተሳሰብና አቋም ያላቸው የሀገሪቱ ህዝብና ምሁራን በእነዚህ ወገኖች የታህሪር አደባባይ አጀንዳን ለማስቀየር ከተቀመረው ከአባይ ፖለቲካ ይልቅ፣ በችግሮቻቸው ላይ ማተኮር ችለው ነበር።

በወቅቱ ስልጣን ላይ የወጣው የእስላማዊ ወንድማማቾች ፓርቲ ህዝባዊ ትግላቸውን እንዳይጠልፍባቸው በራሳቸው የአጀንዳ ትግል ላይ በመጠመዳቸው ሳቢያም፣ የግብፅ ኋላ ቀር ፖለቲከኞችና የያኔው የሙርሲ መንግስት አብዛኛውን የሀገሪቱን ዜጎች በፀረ-ኢትዮጵያ አጀንዳ ዙሪያ አነሳስቶ ለማሰባሰብ ያደረጉት ጥረት ሊኮላሽ ችሏል። ያም ሆነ ይህ ግን በ21ኛው ክፍለ ዘመን እየኖሩ በቅኝ አገዛዝ ዘመን ውሎች ለመተዳደር የሚከጅሉት እነዚህ የግብፅ ውህዳን ፖለቲከኞች፣ ዕውን የህዳሴውን ግድብ ለማስቆም ጊዜው ባለፈበት ፖለቲካ እየተመሩ በባዶ ሜዳ ላይ "ጠብ ያለሽ በዳቦ" በማለት  የደረደሯቸው የቀረርቶና የፉከራ አማራጮች አልሰሩም። ማንም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው ያለፉት የግብፅ መሪዎች ሀገራችን የዓባይን ወንዝ ገድባ እንዳትጠቀም ያልቀመሩት የሴራ ዓይነት አልነበረም።

ከእነዚህ እኩይ ተግባራት ውስጥ ዛሬ ላይ ያረጀውና ያፈጀው አስተሳሰብ ባልለቀቃቸው የሀገሪቱ ፖለቲከኞች የተቀነቀኑት ‘ሰላዩችን በመላክ ግድቡን እናደናቅፋለን፣ ኢትዮጵያ ግድቡን እንዳትገነባ ከጎረቤቶቿ በማናቆር እናዳክማታለን’ የሚሉ አሳፋሪና የጋራ ተጠቃሚነት ከፍተኛ ቦታ በሚሰጠው በዚህ ክፍለ-ዘመን ተቀባይነት የሌላቸው አባባሎች ተጠቃሽ ናቸው። ይሁንና ይህ አስገራሚ አባባል አንድም የሀገራችንን ሰላም ፈላጊ ህዝቦች ማንነት ካለማወቅ፣ ሁለትም የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን እጅ ለእጅ ተሳስሮ በጋራ የማደግ ፍላጎት ካለማወቅ የመነጨ እንደሚሆን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ምክንያቱም የሀገራችን መንግስትና ህዝቦች ጎራው ጭር ሲል ከማይወደው የኤርትራ መንግስት በስተቀር፣ ከሌሎቹ የቀጣናው ሀገራት ጋር በሰላም ተከባብረው ከመኖር ባሻገር ለሰላማቸው ሌት ተቀን የሚሰሩና ዘመኑ ከፈጠረው በጋራ የመልማት ትሩፋት ለመቋደስ በምጣኔ ሀብት ትስስር የተጋመዱ በመሆናቸው ነው። እናም ሀገሮቹ የአንዱ ሰላም እጦት በሌላው የማደግ ትልም ላይ አሉታዊ አሻራ እንደሚያሳርፍ ስለሚገነዘቡ የግብፅ እኩይ ሴራዎች በራቸውን የሚከፍቱ አይመስለኝም። ምክንያቱም ሀገራችን ከአስመራው የሽብር አጋፋሪ መንግስት በስተቀር ከሁሉም ጎረቤቶቿ ጋር በጋራ ተጠቃሚነትና እጅ ለእጅ ተያይዞ በማደግ መርህ ላይ የተመሰረተ እጅግ መልካም የሚባል ግንኙነት ያላት በመሆኗ ነው።

ታዲያ ምናልባትም ውህዳኖቹ አል-ሸባብ በሚገኝበት ሶማሊያ በኩል ይህን ነባራዊ ሁኔታ ተላልፈው ሴራቸውን በሶማሊያ በኩል እንፈፅማለን ቢሉም የሚሳካቸው አይመስለኝም። ለምን ቢሉ ሀገራችን ከሶማሊያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ጋር በህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና በሰላም ላይ የተመሰረተ የጠበቀ ቁርኝት ያላት በመሆኑ እንዲሁም አል-ሸባብ ሀገራችን ውስጥ ምንም ዓይነት የሽብር ተግባር መፈፀም የማይችልበት ሁኔታ በመኖሩ ነው። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ የዚያች ሀገር ህዝቦች ለ21 ዓመታት ያህል በሰላም እጦት ምክንያት ሲወድቁና ሲነሱ እንዲሁም በስደት ሲንገላቱ በ‘አይዞአችሁ’ ባይነት ከጎናቸው የነበሩና ህዝቡንም ተቀብለው እንደ ዜጋ መጠለያ በመስጠት ያደረጉትን ወንድማዊ ክብካቤ መጥቀስ የሚቻል ይመስለኛል።

ይህም ወንድም የሆነው የዚያች ሀገር ህዝብ ሀገራችንን እንደ ሁለተኛ ቤቱ በመቁጠር ችግሮቹን እንዲወጣ አስችሎታል። የሀገራችን መንግስትና ህዝብ በዚህ ሰናይ ምግባራቸው ሳይወሰኑ የአካባቢው የሰላም ጠንቅ የነበሩትን እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረትንና አል-ሸባብን በማስወገድና በማዳከም ብሎም ትርጉም የሌላቸው ደረጃ እንዲደርሱ በማድረግ

ረገድም የማይተካ ሚና ተጫውተዋል። ይህን ዕውነታ ደግሞ የሶማሊያ መንግስትም ይሁን ህዝቡ በሚገባ የሚገነዘቡት መሆኑንም ጭምር። እናም ይህን ወንድማዊ ድጋፍ የተገነዘበ መንግስትና ህዝብ ደግሞ የግብፅን የሴራ አማራጭ ባለውለታ በሆነው በገዛ ወንድሙ ላይ ለማካሄድ ይዘጋጃል ማለት ዘበት ነው—አበው "የህልም እንጀራ" የሚሉት ዓይነት። ግብፆቹ ከሶማሊያ አንፃር በሌላው ዘውጉ በሴራ ትግበራ አማራጭነት አሸባሪውን አል-ሸባብን ለመጠቀም ካሰቡ ደግሞ ከኢትዮጵያ በፊት የሚጎዱት ራሳቸውን ይመስለኛል።

ለዚህ አባባሌ ሚዛን የሚደፉ ተጨባጭ ሃቆችን በምክንያትነት ማንሳት እችላለሁ። እነርሱም በመጀመሪያ ደረጃ አሸባሪው ቡድን በራሱ ህዝብ ላይ በፈፀመውና በሚፈፅመው ኢ-ሰብዓዊ ተግባር የተተፋና በአሁኑ ወቅት አከርካሪው ተመትቶ በእጅጉ መዳከሙና ለጥቆም ቡድኑ በምስራቅ አፍሪካ የአሸባሪው የአል-ቃዒዳ ክንፍ መሆኑን ያወጀ እንዲሁም የግብፅ መንግስት አጋር የሆነው የዋሽንግተን አስተዳደር በአሸባሪነት የፈረጀው ስለሆነ ነው። ከዚህ በመነሳትም የተዳከመውና በህዝብ የተተፋው የግብረ-ሽበራው ቡድን የግብፅን የሴራ አማራጭ ለመተግበር ይችላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ይመስለኛል። ምክንያቱም በሀገሩ ህዝብ ላይ በሚያካሂደው ኢ -ሰብዓዊ ድርጊት ሳቢያ በዚያች ሀገር ዜጎች የተተፋው ቡድኑ፤ የሰው ኃይል የሌለው፣ ለፅንፈኝነት ሥራው የሚጠቀምበትን መሣሪያና የሎጀስቲክስ አቅርቦት የሚያሟላበት ኢኮኖሚያዊ አቅሙ የላሸቀ እንዲሁም በአፍሪካ ህብረት ኃይሎች በየጊዜው በሚደርስበት ወታደራዊ ኪሳራ ሳቢያ አቅሙ ከትናንት ዛሬ የሰለለ መሆኑ ለግብፅ እኩይ ሴራ ብቁ አይደለም፡፡

ምናልባትም ቡድኑ ሴራውን እንዲፈፅም በግብፅ በኩል ቢመረጥ እንኳን በአሮጌ አስተሳሰብ የሚመሩት አዲሶቹ የግብፅ ፖለቲከኞች የሚጣሉት ከሶማሊያ ፌዴራላዊ መንግስት ባሻገር ከአፍሪካ ህብረት ጋር ጭምር መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ጉዳይ ነው—የሞቃዲሸው መንግስትና ህብረቱ እየተፋለሙት ላለው የሽብር ቡድን ድጋፍ ማድረግ ማለት ፀቡ ከሰላም ወዳድ ኃይሎች ጋር ነውና። ከዚህ ጎን ለጎን አሸባሪው አል-ሸባብ የአል-ቃዒዳ ክንፍ ከመሆኑም በላይ፤ የአሜሪካ መንግስት በግልፅ ይህንን ቡድን በአሸባሪነት መፈረጁ የግብፅ ገዥ መደቦች ፍላጎትን መና ማስቀረቱ አይቀሬ ነው። ለምን ቢባል፤ የግብፅ ኋላቀር ፖለቲከኞች ኢትዮጵያን ለማተራመስ ከአሸባሪው ቡድን ጋር ለመስራት የሚፈልጉ ከሆነ በምዕራቡ ዓለምም ይሁን በሌሎች ሰላም ወዳድ ሀገራት መወገዛቸው ስለማይቀር ነው። ከመወገዝም አልፈው እንደ ኤርትራ መንግስት "የሽብር አጋፋሪዎች" ተብለው ወፋፍራም

ማዕቀቦችም ሊጠብቋቸው ይችላሉ። ታዲያ ከእነዚህ መሰረታዊ ሃቆች በመነሳት ለኢ-ፍትሐዊ የውሃ አጠቃቀም ሲባል የተዶለተው የካይሮዎቹ ሴረኞች ዘመን ያለፈበት ኋላ ቀር አስተሳሰብ ውሃ የሚበላው መሆኑ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም– የህቡዕ ተግባሩ አማራጮች የክፍለ-አህጉሩን አዲሱን ሁለንተናዊ ትስስር ያላገናዘበ አሊያም የማያውቅ ደመ-ነፍሳዊ ስሌት ነውና።

እርግጥ እነዚህ የግብፅ ኋላ እሳቤ አቀንቃኞች ሁሌም ቢሆን ቀጣናውን የሚያውክ ሴራን ካገኙ አንዳች “ዕፅ” የወሰደ ያህል መላው የሽብር አካሉ የሚነቃቃውንና ኢትዮጵያን ለማተራመስ የግብፅን አጀንዳ በመልዕክተኝነት ይዞ የሚንቀሳቀሰውን የኤርትራን መንግስት በአስፈፃሚነት ቢይዙም አልቀናቸውም። ምክንያቱም ሻዕቢያም ይሁን በጉያው አቅፎ የያዛቸው አፍራሽ ተቃዋሚዎች የግብፅን የሴራ አጀንዳ የማስፈፀም ብቃቱም ይሁን አቅሙም የላቸውም።

ከተላላኪው የአቶ ኢሳያስ መንግስት ብንነሳ እንኳን፣ የአስመራው ስርዓት ስጋው አልቆ በአጥንቱ በመሄድ ላይ ስለሆነ እንኳንስ መልዕክቱን በአግባቡ ሊያደርስ ቀርቶ ራሱን መቻል አቀቶት እየተንገዳገደ ይገኛል–ከፃዕረ-ሞቱ ጋር ትንቅንቅ እያደረገ ነው ቢባልም ያስኬዳል።የአስመራው የሁከት ቡድን በሀገር ውስጥ አፋኝ፣ ፈላጭ ቆራጭና ፀረ - ዴሞክራሲያዊ በመሆኑ በገዛ ዜጎቹ እጅግ የተጠላ ነው፡፡ አገዛዙ ኤርትራን በሰብዓዊ መብት ረገጣ ግንባር ቀደም ሀገር እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ሥርዓቱ በግለሰቦች የሚመራ ነው፡፡ ምርጫ ብሎ ነገር የለም፡፡

ግና እነዚህና ሌሎች መሰል ችግሮች ተደማምረው ወደ ገደል እየገፉት ያለው ሻዕቢያ፣ የውስጥ ጉዳዮንና እየሻገተ ያለውን ህልውናውን ለመሸፋፈን እንኳን ያልቻለ መንግስት ነው። እናም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኤርትራዊያን ለሻዕቢያ ያላቸው ጥላቻ ከምንጊዜውም የመረረ እየሆነ መምጣቱና ህዝባዊ ድጋፍ በማጣቱ ሳቢያ እርቃኑን እየቀረ ነው፡፡ ለወትሮው ውጭ ከሚገኙ ዜጎቹ በግዳጅ በሚሰበስበው የሁለት በመቶ የገቢ ቀረጥ ገንዘብ ሽብርን የሚመራው፣ የሚያስለጥነውና የሚያስታጥቀው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር፣ በአሁ ወቅት የሁከት አጀንዳው ፍርጥርጥ ብሎ በመታወቁ ሁሉም ዜጋው አይንህ ላፈር እያለው ነው፡፡ አንዳንድ ሀገራትም ለሽብር ተግባር ቀረጥ ሲሰበስቡ ያገኟቸውን የኤርትራን ቆንስላዎች እስከማባረር ደርሰዋል–በአንድ ወቅት ካናዳ ‘በተመድ የፀጥታውን ምክር ቤት

ውሳኔ በመጣስ ቀረጥ ሲሰበስቡ አግኝቻቸዋለሁ’ በማለት ከሀገር ያባረረቻቸውን የሻዕቢያ ቆንስላ ያስታውሷል!

ዛሬ በሻዕቢያ ምክንያት የኤርትራ ኢኮኖሚ ከመዳከም አልፎ በፈጣን የቁልቁለት ጉዞው ወደር አልተገኘለትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ መገለሉን የሚታደግለት አውድና ለጥፋት ተልዕኮው የሚውል የፋይናንስ ድጋፍ የሚያገኝበት ዕድል የለውም። እናም ምናልባት ለግብፅ ገዥ መደቦች ተላልኮ አንዳንድ ፀረ - ኢትዮጵያ ሃይሎችን በማሰበሰብ አንድም ለብቸኝነቱ ወዳጅ ቢያፈላለግ አሊያም ምፅዋትን ላማትር ቢልም ውስጣዊ ችግሮቹና ውጫዊ ተፅዕኖዎች ይገድቡታል። ስርዓቱ በማንኛውም ጊዜ በወታደሮች ሊገለበጥ የሚችል መሆኑ ፍንጭ ከታየ በኋላም፤ የላሸቀ ኢኮኖሚውንና የሌለ ተቀባይነቱን በመያዝ አንገቱን ቀብሮ እየኖረ ያለ ስለሆነ የመልዕክተኝነት ተግባሩን የመፈፀም ብቃትና አቅም የለውም።

ይሁን እንጂ ምናልባትም የአቶ ኢሳያስ መንግስት ልክ እንደ ሆስኒ ሙባረክ ዘመን ሎጀስቲካዊ ድጋፍ ተገፋፍቶ እንዳደረገው ወረራ፤ አሁንም ሳት ብሎት የግብፅን አንዳንድ ፖለቲከኞች ያረጀ አስተሳሰብ በመደገፍ በሚሰጡት ምፅዋት ተገፋፍቶና የልብ ልብ ተሰምቶት ለሁለተኛ ጊዜ ቀጥታ ቀጥታ ወረራ ከፈፀመ፣ በግሌ ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ያሉትን ላስታውሰው እሻለሁ—“ለሶስተኛ ጊዜ እንዳይወረን እናደርጋለን” ያሉትን። ከዚህ መሳ ለመሳም የኪራይ ሰብሳቢነት አኮፋዳውን ለመሙላት ሲል የግብፅ ነጭ ለባሽ በመሆን እንደ አሮጌ ዕቃ ከወዳደቁበት ቦታ ለቃቅሞ ያሰለጠናቸውንና ያስታጠቃቸውን ፀረ-ሰላም ሃይሎችንና አሸባሪዎችን ወደ ሀገራችን አስርጎ በማስገባት የልማት ትልሞቻችንን ለማደናቀፍ ከሞከረ፤ ጀግንነቱን በሚያወቀው ሰራዊታችን አማካኝነት ተመጣጣኝ እርምጃ እንደሚጠብቀው መዘንጋት ያለበት አይመስለኝም። እናም የአስመራው አስተዳደር አንድም በዓለም አቀፉም ይሁን በአፍሪካ ህብረት እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት (ኢጋድ) ተቀባይነት የሌለው፣ ሁለትም የገንዘብ ምንጩ የደረቀ፣ ሶስትም በሥራዊቱ ሳይቀር ጫና እየደረሰበት በመሆኑ ለግብፅ ፖለቲከኞች የሚያደርግለት ጠብ የሚል ነገር አይኖርም፡፡

ይልቁንም የግብፅ ኋላ ቀር ፖለቲከኞችና ባረጀ ጭንቅላት የሚያስቡ አንዳንድ የአዲሱ መንግስት ባለስልጣናት ከዚህ ዓይነቱ ጠብ-አጫሪ ቡድን ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት በቀጣናው ሀገራት እንዲጠሉ የሚያደርጋቸው መሆኑን ቢረዱት ማለፊያ ይመስለኛል።

ለምን ቢሉ፤ በራሱ ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ በቫይረስ ተጠቅቶ በቋፍ ላይ በሚገኘው የኤርትራ መንግስት አማካኝነት ኢትዮጵያን ለማተራመስ ማሰብ፤ የድርጊቱ ቋያ እሳት ገፈት ከአስመራ እስከ ካይሮ ሊደርስ የሚችል በመሆኑ ነው። የአቶ ኢሳያስ መንግስት እያደር እንደ ካሮት በሚያቆለቁለው ኢኮኖሚው አስመራና አካባቢው ሰብስቦ የያዛቸው ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎችም ሆኑ በሁለት ቢላዋ በይነት ተቃዋሚ ሆነው የተሰለፉ ወገኖች፤ የግብፅን ውህዳን ፖለቲከኞች መልዕክት ተቀብሎ የማስፈፀም ብቃትና አቅም የላቸውም። ምክንያቱም እነዚህ ተላላኪዎች በሀገር ውስጥ ተቀባይነት የሌላቸው ከመሆናቸውም በላይ፣ ያነገቡት ምንም ዓይነት ዓላማ ስለሌላቸው መሰል መልዕክቶችን ይዘው ሀገር ወደ ሀገር ቤት ሲያመሩ መንገድ ላይ በሰላም ወዳዱ ህዝብና በፀጥታ ሃይሎች ትብብር በቀላሉ እየተያዙ አሊያም ራሳቸው እጃቸውን እየሰጡ በመመናመናቸው ብሎም ትርጉም ወደሌለው ደረጃ በመድረሳቸው ነው።

ምናልባት ለግብፅ የአሮጌ አስተሳሰብ ገዥዎች የሚጠቅቸው ከሆነ አስመራ የሚገኙት ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎችና አፍራሽ ተቃዋሚዎች ምን ያህል ‘እዚህ ግቡ’ የማይባሉ እንደሆኑ በማሳያነት የአንዱን ተላላኪ ውድቀት ለመላክት–ካይሮ ውስጥ የግብፅን ባንዲራ አንግቦ “የግብፅን ጥቅም ስለሚጎዳ የህዳሴውን ግድብ እንቃወማለን” በማለት በጉዳዩ ላይ የመልዕክተኝነት ስራውን በአሳፋሪ ሁኔታ ስለጀመረው አሸባሪው “ኦነግ።” ራሱን “ኦነግ” እያለ የሚጠራው ይህ የሽብር ቡድን በሀገራችን ህዝቦች በአሸባሪነት ተግባሩ በጥብቅ የሚፈለግ ከመሆኑም በላይ፤ የዓላማ ፅናት ስለሌለው በአሁኑ ወቅት እንደ ገና ዳቦ ስንት ቦታ እንደተቆራረሰ የሚያውቀው እርሱና ፊታውራሪው ኢሳያስ አፈወርቂ ብቻ ናቸው። እኔ እስከማወቀው ድረስ ግን የገለታ ዲልቦ ኦነግ፣ የሌንጮ ለታ ኦነግ እና የብ/ጄኔራል ከማል ገልቹ ኦነግ...ወዘተ. በሚል ተሰነጣጥቋል። ምናልባትም የስንጥቁ ስፋት ከዚህ በላይ ሊሆን ይችላል። እርግጥ የአስመራው የሁከት አስተዳደር አንዳንድ ሀገርን የካዱ ተሰንጣቂ የኦነግ አባላትን የቁም እስረኛ እያደረገ መሆኑ እየተነገረ ነው።

ታዲያ እነዚህ ሁኔታዎች “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ የሽብር ቡድኑ በጀግናው መከላከያ ሰራዊታችን ተመትቶ ከመመናመኑ ባሻገርም ትርጉም ወደ ሌለው ደረጃ እንዲደርስ አድርገውታል። እንዲህ ዓይነቱ ዓላማ የሌለው፣ ጥቅም የማይሰጥና የተዳከመ የጥቂት ጠባቦች ቡድን የአንድ ሰው የእጅ ጣት ያህል ሆኖ ሀገር ውስጥ ቢገባም ቀደም ሲል በህዝቡ ላይ በፈፀመው ጭፍጨፋ ምክንያት ስለተተፋ እንደለመደው በሰላም ወዳዱ

ህዝባችን እየታነቀ ለፀጥታ ሃይሎች የሚሰጥ አሊያም በክንደ ብርቱው መከላከያ ሰራዊታችን ድባቅ መመታቱ አይቀሬ ነው። እናስ እንዲህ ዓይነቱ ብቃትም ይሁን አቅም የሌለው የግብረ-ሽበራ ቡድን የግብፅን ኋላ ቀር ፖለቲከኞች የትርምስ አጀንዳን ያስፈፅማል ተብሎ ይታሰባልን?–ኸረ በፍፁም። በመሆኑም ውህዳኑ ግብፃዊያን ይህ የሽብር ቡድንም ይሁን ሌሎች ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ምንም ነገር እንደማይፈይዱላቸው ተገንዝበው ፊታቸውን ወደ ሰለጠነው የክፍለ ዘመኑ በመግባባት በጋራ የማደግ አስተሳሰብ መምጣት ያለባቸው ይመስለኛል–ለሴራቸው ያሰቧቸው ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ምራጮች እንጂ ተመራጮች አይደሉምና።

እስቲ አሁን ደግሞ ውህዳኑ የግብፅ ኋላ ቀር አስተሳሰብ አራማጆች ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ኃይሎች በአማራጭነት ተሞክረው ካልሰሩ በግድቡ ላይ ቀጥተኛ ጥቃት መሰንዘር እንደሚችሉ ያወሩ ስለነበረው የጦረኝነት አስተሳሰብ እናምራ። እርግጥ ጦርነት አውዳሚና ለየትኛውም ወገን ጠቃሚ ያልሆነ ተግባር መሆኑን የአሮጌ ዘመን እሳቤ አቀንቃኞቹ ውህዳን ግብፃውያን የሚስቱት አይመስለኝም። በልማት፣ ተባብሮ በመስራትና አንዱ ለሌላኛው ሀገርና ህዝብ በማሰብ እንጂ፤ በጦርነት የተገነባ ሀገርና ህዝብ የለም። እናም ዛሬ በዘመነው ዓለም ውስጥ ጦርነት እንደ አማራጭ የሚወሰድበት ሁኔታ እየቀረ በመጣበት ጊዜ፤ ኋላቀሮቹ የግብፅ ፖለቲከኞች ግን ይህን ክቡሩን የሰውን ልጅ ህይወት የሚቀጥፈውን እንዲሁም ሀብትና ንብረትን የሚያወድመውን ድርጊት እንደ አግባብ ያለው አማራጭ ለማስቀመጥ መሞከራቸው አስገራሚ ነው።

ለነገሩ ኢትዮጵያዊያን ከአበው ጀምሮ የሚታወቁት በሰላም ፈላጊነታቸው ነው። ከሰላም ፈላጊነታቸው ባሻገርም ለሀገራት ሰላም መጠበቅ ቁርጠኛ አቋም በመያዝ ህይወታቸውን ጭምር እየከፈሉ ከትላንት ዛሬ ላይ የደረሱ ህዝቦች ናቸው። ይሁንና ከዚህ የማይናወጥ የሰላም አቋማቸው በመለስ ጦር ሰብቆ ለመጣባቸው ለየትኛውም ሀገር ዛቻና ፉከራ ተንበርክከው አያውቁም። ቢንበረከኩ ኖሮ ዛሬ ያለችውን ነፃ፣ ሉዓላዊት፣ የፈጣንና የተከታታይ ዕድገት ባለቤት የሆነች ሀገርን መፍጠር ባልቻሉ ነበር። ይህን ሃቅ ደግሞ የግብፅ ወንድሞቻችን ከትናንት እስከዛሬ ድረስ ባለው ማንነታችን ጠንቅቀው የሚያውቁት ይመስለኛል። አንዳንድ የታሪክ ምሁራን እንደሚገልፁት ግብፆች ሀገራችንን ከ14 ጊዜ በላይ በቀጥታ ወርረዋል። በቀጥታም ተሸንፈዋል። ከእነዚህ ወረራዎች ውስጥ አንዱ እ.ኤ.አ. በ1869 በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት ወቅት የተካሄደው የጉራዕ ጦርነት ነው።

ይሁንና በወቅቱ ጦርነቱን ይመሩ በነበሩት በራስ አሉላ አባነጋ አማኝነት ግብፆች ለወሬ ነጋሪ ሳይቀሩ እንዲበታተኑ ተደርገው ድል ተነስተዋል።

ያም ሆን ይህ ዛሬም ቢሆን ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጡት ሀገራችንና ህዝቦቿ 'ውሃን በደም እንለውጣለን' የሚሉ የግብፅ ኋላቀር ፖለቲኞች፣ በተቃዋሚዎች አሊያም ሁከት በሚያማልለው የኤርትራ መንግሰት አማካኝነት የወጠኑትን የእጅ አዙርም ይሁን ቀጥተኛ ጥቃት በብቃት የመመከት ችሎታ ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም አሸባሪዎችንና ፀረ-ሰላም ሃይሎችን በመጠቀም የግድቡን ስራ ለማደናቀፍ የሚደረግ ሙከራ ሊሳካ የሚችልበት ዕድል አለመኖሩን ማወቅ ብልህነት ይመስለኛል። እናም ሀገራችንና ህዘቦቿ ከማንም ፉከራና ቀረርቶ ባሻገር የህዳሴውን ግድብ መገንባታቸውን ይቀጥላሉ፤ ከሰማይ በታች የሚያግዳቸው አንዳችም ኃይል የለም። እናም ሰሞኑን ፕሬዚዳንት አል-ሲሲ በዓባይና በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ ከኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ጋር ያደረጉት የመግባቢያ ስምምነቶች ትክክለኛ መንገድ ነው። ሁለቱንም ሀገራት ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚያሸጋግር እሳቤ።

እርግጥ ቀደም ሲል ሀገራችን በነበረባት ድህነትና የአስተሳሰብ ውስንነት ሳቢያ አባይን ለልማት ሳታውል ቀርታለች—በዘመኑ የነበሩት የግብፅ ገዥዎች በኢትዮጵያዊያን ላይ ይሰነዝሩት የነበረው ቁጣና ዛቻ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለቴ ነው። ይሁንና ዛሬ እነዚህ የድህነትና የአስተሳሰብ ውስንነት ተግዳሮቶች በኢፌዴሪ መንግስት ውጤታማ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በሚመራው ታታሪው የሀገራችን ህዝብ አማካኝነት ተሰብረዋል። በዚህም የዓለም የምጣኔ ሀብት ዕድገት ተምሳሌት መሆን ችለናል። ይህ ምቹ ሁኔታም በራሳችን ወንዝ ላይ በራሳችን ሀገራዊ ጥቅም በመተማመን የህዳሴውን ግድብ ለመገንባት አስችሎናል። ግድቡ ከጫፍ እስከ ጫፍ ለግንባው በተንቃነቀው መላው የሀገራችን ህዝብ ገንዘብ የሚሰራ እንደመሆኑ መጠን፤ በእርሱው ጠባቂነት የሚሰራ ነው። እናም በየትኛውም መንገድና በሌሎች አፍራሽ ስልቶችን ለመጠቀም የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አይፈቅድም። ቢሞከርም ቀዳዳዎች ሁሉ ዝግ መሆናቸውን ማወቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ዘመኑ ያለፈበትን የፖለቲካ ጨዋታ በመጠቀም ወይም በዛቻና በማስፈራራት አባይን እንደ ትናንቱ የግሌ ነው ለማለት መሞከር በአዲሷ ኢትዮጵያ ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ አንድም ጋት ሊያስኬድ ስለማይችል ነው።

እናም ከእነዚህ አሮጌና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እሳቤዎች ይልቅ፤ ሁሉንም የተፋሰሱን ሀገሮች በፍትሐዊነት የሚጠቅመውንና ዘመናዊውን የመወያየት፣ የመረዳዳትና እኩል አሸናፊ የመሆን ጥበብን መከተል አዋጭ መንገድ ነው። ስለሆነም አዲሱ ፕሬዚዳንት አል-ሲሲ በኢኳቶሪያል ጊኒ-ማላቦ ውስጥ መግባባት ላይ የደረሱባቸው ስምምነቶች በአዲስ ምዕራፍና በቀና መንፈስ እጅ ለእጅ ተያይዞ አብሮ ለማደግ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ዘልቆ መስራት ይገባል ባይ ነኝ። አበቃሁ።